## መልመጃ አንድ÷ ተዋንያን
**Exercise One: Actors**

1. እምዬ ማን ናቸው?
2. የዳኛው ሚና ምንድን ነው?
3. ምንተስኖት ማን ነው?
4. እንደልቡ ተግባሩ/ሥራው ምንድን ነው?
5. እምዬ እና ገለታ ለምን ተጣሉ?
6. ገለታ ማን ነው?
7. ገለታ የማንን መሬት ነው በተጨማሪ የሚያርሰው?
8. የዳኛው ፍርድ/ውሳኔ ምን ይመስላል?
9. ስንት ተዋናንያን ተሳትፈዋል?
10. ጥጋበኛ የተባለው ማን ነው?

## መልመጃ ሁለት÷ምንባብ ÷ትክክለኛውን መልስ ከ ሀ÷ ለ እና ሐ ምረጡ
**Exercise Two: Reading Comprehension. Choose the right answer between A, B, and C.**

1. ከማሳዬ ብትወስድ የሚለው ሐረግ የቱን ይተካል?

ሀ. ከእኔ ቆርሰህ ብታርስ

ለ. የእኔን ድርሻ ሳትነካ

ሐ. ከእኔ መሬት ተሻምተህ ለአንተ ብታደርግ

2. እፊትህ ያለ ጊዮርጊስ ይፍረድ ይፋረድ ምን ማለት ይመስላችኋል?

ሀ. እፊታችን ያለው ታቦት እውነቱን ይመስክር

ለ. ታቦቱ የተስተካከለ ፍርድ ይስጥ

ሐ. ሁለቱም ትክክል ናቸው

3. "ጽድቁ ቀርቶ በወጉ በኮነነኝ" ምን ማለት ነው?

ሀ. መግደልም ቢሆን በሥርዓቱ ባደረገልኝ

ለ. ትክክለኛው ፍትህ ቀርቶ የተገባውንም በሥርዓት ካደረገልኝ እመርጣለሁ

ሐ. ሀ እና ለ

4. ምርር የሚለውን ቃል________ ይተካል።

ሀ. ስቅቅ እና ልብን በሚሰብር ሁኔታ

ለ. በደስታና በፈገግታ

ሐ. ቀለል ባለ ሁኔታ

5. ሁለቱ ሲጨቃጨቁ

ሀ. ክፉና በጎውን ሲነጋገሩ

ለ. ሲደባደቡ

ሐ. ጻኛ ፊት ቆመው ሲሟገቱ

6. የምተገትግህ የሚለው ቃል ትርጉሙ ምን ማለት ነው?

ሀ. የምገርፍህ

ለ. የምሰድብህ

ሐ. የምመታህ

7. የእርጎ ዝንብ በማያገባው ሁሉ________ ማለት ነው::

ሀ. እዚያም እዚህም ጥልቅ የሚል

ለ. ቀዥቃዣ ጥልቅ የሚል

ሐ. ሁለቱም ትክክል ናቸው

8. በፈረሰኛው ጊዮርጊስ ____________የሚለውን ይተካል::

ሀ. በፈጣኑና በቶሎ ሰሚው ታቦት

ለ. በፈረስ የሚጋልብ ሰይጣን

ሐ. ሽምጥ ጋላቢው ሰማዕት

9. ጥጋበኛውና ጉልበተኛው ሲል ምን ማለት ነው?

ሀ. በአንደ በኩል ትዕቢት ሲዋጥረው በሌላ በኩል አምባ ገነን እብሪተኛ ሰው

ለ. ለነፈሱ ያደረሰው

ሐ. ትህትና ያደረበት ሰው

10. እንደ ልቡ የተባለው ማን ነው?

ሀ. የእምዬ እኩል አራሽ

ለ. የጻኛው ገበሬ

ሐ. ሀ እና ለ

## መልመጃ ሦስት፥ በክፍል ሀ ያሉትን ቃላት ወይም አባባሎች ከክፍል ለ ጋር አዛምዱ

**Exercise Three: Match these words or expressions in column A with their equivalent in column B.**

| አምዱ ሀ<br>**Column A** | አምዱ ለ<br>**Column B** |
|---|---|
| 1. የእኩል አራሽ | ሀ. እግዜር ይማርህ ሳይባል |
| 2. ጽድቁ ቀርቶ በወጉ በኮነነኝ | ለ. መሞቻ ጊዜው ያለፈበት |
| 3. ይሳለቅባቸዋል | ሐ. እምቢ አልፈታም አለ |
| 4. ያሾፍብኛል | መ. ቀበሌውን እና ሰፈሩን የሚቆጣጠር |
| 5. አስዋለኝ | ሠ. ይቀልድብኛል |
| 6. ጥጋበኛው መች እሺ አለ | ረ. የሌላውን ማሳ በማረስ እኩል ምርቱን የሚካፈል |
| 7. ሞት የረሳት አሮጊት | ሰ. ሲገርፈው አቆሰለው |
| 8. መልከኛው | ሸ. ጮማ መቁረጡ ቀርቶ ከሽሮ ባገኘሁ |
| 9. ሲለምጠው | ቀ. ፍትህ በመስጠት አስወግድልኝ |
| 10. ሳይታመም ሞተ | በ. ይቀልድብኛል |

## መልመጃ አራት፥ በመዝገበ ቃላት ውስጥ ያሉትን ቃላት በመጠቀም ክፍት ቦታዎችን ሙሉ

**Exercise Four: Fill in the blanks by using words from the glossary**

1. ዕውቅና ተሰጥቶት እና በሚከበረውና በጨርቅ ውይም በወረቀት ላይ ተስሎ በሚቀለም ስም መማጸን __________
2. ከልጥ ወይም ከበሬ ቆዳ ተዘጋጅቶ በሬ የሚገረፍበት __________
3. በሰማዕት ስም መማጸን __________
4. በትንሽ በትንሹ ሳይሆን አከታትሎ ማሳውን ማረስ __________
5. እየከፈለ በትንሽ በትንሹ የሚያርስ __________
6. በማያገባው ሥር ሥር የሚል __________
7. የተኩስ መሣሪያን በደንብ መያዝ __________
8. የነፍስ የነፍሱን __________
9. አይመለከተኝም፥ ኃላፊነትም ተጠያቂነትም የለብኝም __________
10. ከሚገባ በላይ አቆሰለው __________

## መልመጃ አምስት፥ የተሰመሩትን ቃላት በተመለከተ ጥያቄዎች ጠይቁ

**Exercise Five: Ask questions corresponding to the underlined words**

1. ሞት የረሳት
2. ሲጨቃጨቁ
3. ጥጋበኛውና ጉልበተኛው
4. የሰፈሩ መልከኛ
5. ደካማው አቶክታኪ ምንተስኖት
6. ሳይታመም ሞተ
7. ለሚመጣው አደጋ
8. መሬቱን አብስዬ ልረስ
9. የኩል አራሽ
10. ጊዮርጊስ ይፍረድ

## መልመጃ ስድስት፥የማዳመጥ ምንባብ፥ ውይይቱን ተመልከቱና በእያንዳንዱ መሥመር ላይ ያላችሁን አስተያየት ስጡ።

**Exercise Six: Listening comprehension. Watch the conversation and comment each line**

ገለታ - ለመሆኑ በደንብ ለማይታረስ መሬት ምን ዳኛ ያስፈልገዋል? ደንበኛ አራሽ እንጂ በማለት ይሳለቅባቸዋል። በመካከሉ የኩል አራሻቸው ማሳው እየታረሰ መዋሉን አይቶ ሁለቱ ሲጨቃጨቁ ይደርሳል።

ምንተስኖት - አቶ ገለታ በሕግ፥ በባንዲራው የሰው መሬት አትረስ! ፍታ!

እምዬ - በፈረሰኛው ጊዮርጊስ፥ ይኸው ጉልበተኛ ማሳዬን እያረሰ ነውና አስጥለኝ!

ዳኛ - ማን ነው እሱ?

ምንተስኖት - (ጣልቃ ገብቶ) ገለታ ነዋ፥ ጥጋበኛውና ጉልበተኛው! እስከ ዛሬ እየቆረሰ ነበር የሚያርሰው ዛሬ መደዲያውን ማሳውን ተያይዞታል።

እምዬ - ይኸው ባለ ጉልበቱ ማሳዬን እያረሰ ለምን ታርሳለህ ብለው ይብስኑ ያሾፍብኛል።

ምንተስኖት - አቶ ገለታ በሕግ፥ በባንዲራው የሰው መሬት አትረስ! ፍታ!

ገለታ - "የእርጎ ዝንብ" አንተ ደግሞ ምን አገባህ መሬቴን ባርሰው? ሂድ ከዚህ በዚህ በበሬ ጅራፍ ነው የምተገትግህ!

ምንተስኖት - በሉ ተውት እምዬ ወደ ዳኛ እንሂድ ።

ዳኛ - እዩት ይሄን ጥጋበኛ ሳይታመም ሞተ!

ገለታ - የፈለገኝን ይበለኝ ተወው እባክህ!

ዳኛ - "ሥራ ለሠሪው እሾህ ላጣሪው የሚባለውም" ይኸው ነው።

## መልመጃ ሰባት፥ አዎንታ ወይም አሉታ ጥያቄዎች

**Exercise Seven: yes or no questions**

| | አዎን | አይደለም |
|---|---|---|
| 1. እምዬ አሮጊት ናቸው:: | | |
| 2. ዳኛው አራሽ ገበሬ ናቸው:: | | |
| 3. ምንተስኖት ታማኝና ትሁት ሰው ነው:: | | |
| 4. እንደልቡ ጎበዝ ዳኛ ነው:: | | |
| 5. እምዬ እና ገለታ ሰላማዊ ጎረቤታሞች ናቸው:: | | |
| 6. ገለታ ጎበዝና ታማኝ ገበሬ ነው:: | | |
| 7. ገለታ የእምዬን ማሳ በተጨማሪ ያርሳል:: | | |
| 8. ዳኛው ትክክልኛፍርድ/ውሳኔ ሰጥቷል:: | | |
| 9. ገለታ በበሬ ጅራፍ የገረፈው እምዬን ነው:: | | |
| 10.ጥጋበኛ የተባለው ገለታ አይደለም:: | | |

## መልመጃ ስምንት፥ ተቃራኒ የሆኑትን ቃላት በመልመጃው ውስጥ ፈልጉ

**Exercise Eight: Find the antonyms of these words in the text.**

1. መነሳት
2. ጤንነት
3. መደሰት
4. ጥንቃቄ
5. ሀቀኛ/እውነተኛ
6. ኮስታራ
7. ወጣት/ጎልማሳ
8. ስድ/ገላጣ
9. የተበላሸ/ትክክል ያልሆነ
10. ምስኪን

## መልመጃ ዘጠኝ፥ ውይይቱን በራሳችሁ አባባል/ቃላት አሳጥራችሁ ጻፉ

**Exercise Nine: Summarize the dialogue in your own words.**

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

____________________________________________________________________

## መልመጃ አስር፥ ኪነት መሥራት:: ኪነቱን ተለማምዳችሁ የከተማውን አማርኛ በመጠቀም ዝግጅት አቅርቡ:: ይህ ዝግጅት ባህሉን፥ አቀራረቡን እና ሌሎች የቋንቋው ስልቶች እንዲገቡ ያስፈልጋል::

**Exercise Ten: Role play:** Rehearse and perform the skit by using urban Amharic. Be mindful to reflect the local culture, gestures and other kinesics aspects of language